# የአብይም ንጉስ

እነ ጎርፍ አመጣሽ ፣ ቅቤውና ሱሴ
ደርሶ እንደሚመጣው ፣ ሃምሌና ነሃሴ
የትም የበቀሉ ፣ የሆኑ ወፍ ዘራሽ
ሐገርን ታዳጊ ፣ ለኢትዮጵያ ደራሽ
አርገን ተቀብለን ፣ የአፋቸውን ሰምተን
የወያኔ ቅፍቅፍ ፣ ካድሬነት እረስተን
አንድዜ ወደ ቀኝ ፣ አንዴ ወደግራ
እያወዛወዙ ፣ ያሳዩን መከራ
ማስተዋል ተስኖን ፣ ወደኋላ ሳናይ
ዛሬም ፍዳ መቁጠር ፣ በወያኔ ሰላይ ።

የሀሰት ባላባት ፣ ተረት ሲደርቱ
ማስረጃ አያቀርቡ ፣ ተሟግተው አይረቱ
በግንጠላ አበጋዝ ፣ መንጋ ሽማግሌ
በድፍን ደንቆሮ ፣ ጨለማ እንደ ሀምሌ
ባገር የተዘራ ፣ በሽታ ሙጀሌ
በኦነግ አንጋቾች ፣ በወያኔ ሎሌ
ሲቀድስ ያደገ ፣ በወንጌሉ አኖሌ
ሰላምና አንድነት ፣ እርሙ ነው ባተሌ ።

በአናሳነት ደዌ ፣ በሽታ ተስቦ
በፅኑ የታመመ ፣ መንጋ ተሰብስቦ
ቢነገር አይሰማ ፣ የማይፀዳ ታጥቦ
አገር ልምራ ይላል ፣ በውርጋጥ ተከቦ
ያውም በተገንጣይ ፣ ያውም በነ ዝንቦ ።

እነ ሁሉም ኬኛ ፣ እነ ሁሉ ብርቁ
ታሪክና ሐገርን ፣ ጭራሽ የማያውቁ
በማንተታቸው ፣ የሚሽማቀቁ
ከህሊናቸው ጋር ፣ የማይታረቁ
ሊላጩን ይሻሉ ፣ እንዲያው በደረቁ ።

እንዲህ ሆኖ ቀረ ፣ የኛ መጨረሻ
አንድ ጀግና ጠፍቶ ፣ ከምድረ አበሻ
አሻፈረኝ የሚል ፣ መከታና ጋሻ
የጠገበው ሄዶ ፣ በተራበው ውሻ
እዚህ ግባ የማይሉት ፣ ያውም በበሻሻ
ምስኪን ኢትዮጵያዊ ፣ ይጣ ወይ መድረሻ ።

ዘመነ ግርምቢጥ ፣ ነገር ወደ ግራ
ያልሆነ ስም ይዘን ፣ ዘወትር ስንጣራ
ለካስ በጅ አዙር ነው ፣ ሴራው የሚሰራ
በፅንፈኛው ሜንጫ ፣ ሁሉም የሚዘራ
እኛም መስሎን ነበር ፣ ቅቤው የሚመራ
ቤተ መንግስት ያለው ፣ የኦነግ ኩታራ
የአብይም ንጉስ ፣ ጃዋር ነው ሲጣራ ።

ታዛቢው

August 28/ 2019